# መልካም አስተዳደር ለጥቃት ጥበቃ

**የተወሰደው-** *ከመልካም አስተዳደር ለጥቃት ጥበቃ ፦ ለዩናይትድ ኪንግደም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ቦርዶች መመሪያ ፣ ቦንድ ፣* ግንቦት 2019እ.ኤ.አ በቦንድ አሳታሚ ድጋፍ የታተመ ፣ ሶሳይቲ ህንጻ ፣ 8 ኦል ሴይንትስ ጎዳና ፣ ለንደን N1 9RL ፣ዩናይትድ ኪንግደም በዚህ ሊንክ ላይ ይገኛል፦[https://safeguardingsupporthub.org/documents/good-governance-safeguarding-guide-ngos](https://safeguardingsupporthub.org/documents/good-governance-safeguarding-guide-ngos)

ተቋማት ደህንነታቸው የተጠበቁ ይሆኑ ዘንድ ጥሩ የሆነ የመልካም አስተዳደር መዋቅሮችን መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ አጠር ብሎ የቀረበ የሙሉ መመሪያው አጭር ማጠቃለያ፣ የጥቃት ጥበቃን በመምራት ረገድ ቦርዶችን ግንባር ቀደም ከማድረግ አንጻር ሊከተሏቸው የሚገቡ ስድስት አካሄዶችን በተመለከተ አጠቃላይ እይታ ይሰጣል፦ እነዚህ አካሄዶች ከዚህ በታች ባለው ሥዕል/ዲያግራም ተጠቃለው ተቀምጠዋል ፡፡



የማንኛውም ተቋም ባለአደራ ቦርዶች የመጀመሪያው እርምጃ ፣ ከተቋሙ ከፍተኛ አመራር ጋር በመሆን ከሙሉው የጥቃት ጥበቃ መመሪያ አንፃር ያሉትን የተቋሙ ፖሊሲዎች ፣ ሂደቶች እና አሠራሮችን በመገምገም ቀሪ ክፍተቶችን ለመሙላት እና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመተግበር ዕቅድ ማዘጋጀት ሊሆን ይችላል ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የስድስቱ አካሄዶች ማጠቃለያ ከዚህ በታች ባለው ክፍል ቀርቧል፦

# 1. ትክክለኛውን የስራ ድባብ ይፍጠሩ

የጥቃት ጥበቃ በአግባቡ እየተተገበረ መሆኑን ለማረጋገጥ ፣ ተቋማት ጥሩ የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲዎች ፣ አሰራሮች እና ሥርዓቶች ሊኖራቸው ይችላል ፡፡ ሆኖም ግን የተቋሙ የሥራ ባህል ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሠራተኞች ፣ የማኅበረሰቡ ክፍሎች እና ሌሎች አካላት ፣ ነገሮች ሲበላሹ/ሲሳሳቱ፣ ስጋቶቻቸውን ወይም አቤቱታቸውን ለማንሳት/ለማቅረብ ምቾት እንዲሰማቸው እንዲሁም እንደነዚህ ያሉ ስጋቶች በተገቢው መንገድ እርምጃ ይወሰድባቸዋል የሚል እምነት የሚያሳድር አከባቢን/ሁኔታን መፍጠር አለበት ፡፡

ተቋማዊ የሥራ ባህል "ተገቢ እና ተገቢ ያልሆነ ባህሪን የሚያሳዩ የጋራ አመለካከቶች ፣ እሴቶች እና እምነቶች ስርዓት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል (ጄኒፈር ቻትማን ፣ በርክሌይ ካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሃስ ቢዝነስ ት / ቤት የአስተዳደር ፕሮፌሰር )

# 2. የስጋት ተጋላጭነትን መቀነስ

ተቋማት የራሳቸውን ተግባራት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ግለሰቦች እንዴት ተጋላጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ማጤን አለባቸው ፡፡ የበጎ አድራጎት ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት (መያድ) ተቆጣጣሪ ባለሥልጣናት የጥቃት ጥበቃ መስፈርቶችን ሲያስተዋውቁ ያካተቱት ጉዳይ የተቋማት ቦርድ ስጋቶችን በንቃት ለመቆጣጠር ከሚያከናውናቸው ሥራዎች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ቁልፍ ተግባር መሆኑን ነው ፡፡ የዚህ አንዱ ማሳያ የእንግሊዝ የበጎ አድራጎት ኮሚሽን መመሪያ (CC26 ፣ የበጎ አድራጎት ተቋማት እና የስጋት ተጋላጭነት አስተዳደር እና የበጎ አድራጎት አስተዳደር ደንብ) ነው ፡፡ ይህም እዚህ ላይ ይገኛል፦ https://assets.publishing.service.gov.uk/government/uploads/system/uploads/attachment_data/file/589944/CC26.pdf

የባለአደራዎች ቦርድ፣" ከእርዳታ ድርጅቱ ጋር የተያያዙ ሁሉንም የስጋት ተጋላጭነቶች በንቃት የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ፣ የጥቃት ጥበቃ ተጋላጭነቶችንም በተመሳሳይ መንገድ የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው ለማሳሰብ በማለት ኮሚሽኑ መመሪያውን በጥቅምት 2018 ላይ ማሻሻያ አድርጓል። ተጋላጭነቶች ተለይተው ከታወቁ በኋላ ብቻ አንድ ድርጅት ያንን ስለመቆጣጠር ማሰብ ይጀምራል ፡፡ "

## 3. መናገርን/ማጋለጥን ማበረታታት

መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ፤የሥነ ምግባር ጉድለት የሚፈጽሙ ወይም ተባባሪ ሆነው የተሳተፉ ሰዎች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ፤ እና ቅሬታዎችን ወይም ስጋቶችን የሚያነሱ ደግሞ በተገቢው ሁኔታ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ክብር የተገባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ሁኔታን ለመፍጠር ሁሉንም ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፡፡

እነዚህ መርሆዎች በሁሉም ፖሊሲዎች ፣ አሰራሮች ፣ የዓላማ መግለጫዎች ፣ እሴቶች ፣ ተልእኮዎች እና የሥነ-ምግባር ህጎች ውስጥ የተዋሐዱ መሆን አለባቸው ፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ የመንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን የሥራ ባህል እና ሠራተኞቻቸውን ወይም አብረዋቸው ከሚሰሩ ሰዎች ወይም ከሚወክሏቸው ሁሉ የሚጠበቅ ሥነ-ምግባርን በግልፅ ማስቀመጥ አለበት ፡፡

ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ፣ ተጠቂዎች ፣ ከጥቃት የተረፉ ሰዎች ወይም ምስክሮች ከ ተቋሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ላይ የደረሰ፤ደርሷል ተብሎ የተጠረጠረ ወይም ሊደርስ የሚችል ጉዳትን/ጥቃትን በድፍረት እንዲናገሩ /እንዲያጋልጡ/ የሚያስችል አሠራሮች ሊኖሯቸው ይገባል ፡፡

## 4. ቅሬታዎችን /አቤቱታዎችን ይመርምሩ

ቅሬታዎች ስለተቋሙ አሠራር ፍንጭ ይሰጣሉ ፡፡ የበላይ አመራር ቡድኑ እና የባለአደራ ቦርድ ፤በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ በመገኘት፤ከተቋሙ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች የሁሉንም ደህንነት ለመጠበቅ እና ከጥቃት ለመከላከል የተቀመጡ ሥርዓቶች እና ጥበቃዎች በተገቢው ሁኔታ/ያለክፍተት እየተገበሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ አይችሉም ፡፡

ስለሆነም አብዛኛውን ጊዜ የጥቃት ክስተቶችን፣ ቅሬታዎችን እና ስጋቶችን በመመርመር ነው የደረሰ ወይም ሊደርስ የሚችል ጉዳት እና / ወይም የሥነ-ምግባር ጉድለ በግልፅ የሚወጣው/የሚጋለጠው እንዲሁም በተገቢው መንገድ ምላሽ የሚሰጠው እና ለመቆጣጠር የሚቻለው ፡፡

እንደስጋቱ አይነት እና ማን ጉዳት ደረሰበት/ተጠቂ ነው/ የሚለው ጉዳይ ላይ በመመርኮዝ የጥቃት ክስተቶች በተለያዩ መንገዶች ይጋለጣሉ፡፡

## 5. ከጥቃት ለተረፉ ግለሰቦች ድጋፍ ያድርጉ

የባለአደራዎች ቦርድ ተቋሙ ከጥቃት የተረፉትን ግለሰቦች ማዕከል ያደረገ አቀራረብ መከተሉን ማረጋገጥ አለባቸው። ይህ ከጥቃት የተረፈ/ች ግለሰብን ሁለንተናዊ ደህንነት እና ፍላጎት ማረጋገጥ ሁሉም እርምጃዎች ማዕከል የሚያደርጉት ጉዳይ ነው ፡፡

## 6. ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን ያበረታቱ/ያስፍኑ

ግልጽነት እና ተጠያቂነት የአንድ ተቋም መስተዳደር መሠረታዊ መርሆ መሆን አለበት ፡፡ የዩናይትድ ኪንግደም የበጎ አድራጎት መስተዳደር ደንብ ይህንን ሲያብራራ "ቦርዱ ድርጅቱን በግልፅነት እና በተጠያቂነት ይመራል ፡፡ ግልጽ ላለመሆን በቂ ምክንያት ከሌለው በስተቀር የበጎ አድራጎት ተቋሙ ስለሚሰራው ስራ በሩ ክፍት ነው ፡፡"

ከዚህ መርህ በስተጀርባ ያለው ምክንያት የሚከተለው ነው፡-"አንድ የበጎ አድራጎት ተቋም የህዝብን ጥቅም እያስጠበቀ ነው የሚለው ጉዳይ የህዝቡን አመኔታ ለማግኘት እና ለተቋሙ ስም እንዲሁም ለስኬቱ መሠረታዊ ነው ፣ ሰፋ ሲልም አጠቃይ የዘርፉ ስኬት ነው ፡፡ ስኬትን በሚያከብር እና ከስህተቶች ለመማር ፈቃደኛ በሆነ፣ እውነተኛ እና ግልጽ በሆነ የሁለትዮሽ ግንኙነት አማካኝነት ተጠያቂነትን እውን ማድረግ፣ ታማኝነትን እና መተማመንን ለመገንባት እና ህጋዊነትንም ለማግኘት ይረዳል ፡፡"

ስለሆነም የባለአደራዎች ቦርድ ፣ርዕሰ ጉዳዩ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልግ መሆኑን እና የተጎዱት ወገኖች መብት እና ደህንነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ተቋሙ ተገቢውን ግልፅነት እና ተጠያቂነትን እንዴት ማስፈን እንደሚችል ማጤኑ አስፈላጊ ነው ፡፡

## ዋቢዎች

*መልካም አስተዳደር ለጥቃት ጥበቃ ፦ ለዩናይትድ ኪንግደም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቦርዶች መመሪያ* ፣ ቦንድ ፣ ግንቦት 2019፣ ቦንድ ፣ ዩናይትድ ኪንግደም ፡፡ እዚህ ሊንክ ላይ ይገኛል፦ https://safeguardingsupporthub.org/documents/good-governance-safeguarding-guide-ngos

*CC26 ፣ የበጎ አድራጎት ተቋማት ፣ የሲጋት አያያዝ እና የበጎ አድራጎት መስተዳደር ደንብ ፣* የበጎ አድራጎት ኮሚሽን 2017 ፣ የበጎ አድራጎት ኮሚሽን ፡፡ በዚህ ሊንክ ላይ ይገኛል፦
https://assets.publishing.service.gov.uk/government/uploads/system/uploads/attachment_data/file/589944/CC26.pdf

ይህ ሰነድ ከዩናይትድ ኪንግደም መንግሰት በዩኬ ኤይድ በኩል የገንዘብ ድጋፍ ከሚደረግለት ፕሮጀክት የተገኘ ውጤት ነው ፡፡ ሆኖም ግን ፣ በውስጡ የያዘው መ ረጃ እና አመለካከቶች የግድ የእንግሊዝ መንግስት ነው ወይም እርሱ ነው ያጸደቀው ማለት አይደለም ፤እንደነዚህ ላሉት አመለካከቶችም ሆነ መረጃዎች ወይም ለሚጣለው ማንኛውም እምነት/ጥገኝነትም ሃላፊነትም አይቀበልም/አይወስደም ፡፡

ይህ ህትመት በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ብቻ አጠቃላይ መመሪያ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን ሙያዊ ምክርን አያካትትም ፡፡ በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ ግልጽ የባለሙያ ምክር ሳይገኝ ወደ እርምጃ ሊገባ አይገባም ፡፡ በዚህ ህትመት ውስጥ ለተጠቀሰው መረጃ ትክክለኛነት ወይም ሙሉነት ፣ እና በሕግ በተፈቀደው መጠን ይህንን ሰነድ በማዘጋጀት የተሳተፈ ተቋምም ሆነ አካል ማንኛውንም ተጠያቂነት ፣ሀላፊነት ወይም ግዴታ አይቀበልም ወይም አይወስድም ፤በዚህ ህትመት ውስጥ ባለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ እርምጃ ለሚወስድ ወይም በመረጃው ላይ በመመርኮዝ እርምጃ ከመውሰድ ለሚታቀብ ማንኛውም ሰው ተያይዘው ለሚመጡ ጉዳዩች የመንከባከብ ግዴታ ውክልና ወይም ዋስትና (በግልጽ የተቀመጠ ወይም በስውር ) አልተሰጠም ።

**ስለ ጥቃት ጥበቃ መረጃ እና ድጋፍ ማዕከል ፦** የጥቃት ጥበቃ መረጃ እና ድጋፍ ማዕከል በዩናይትድ ኪንግደም የውጭ ፣ የኮመንዌልዝ እና የልማት ጽ / ቤት (FCDO) የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል ፡፡ የጥቃት ጥበቃ መረጃ እና ድጋፍ ማዕከል አገልግሎቶች ፣ የጂሲፒ አማካሪ (GCPS) ፣ ቴሬ ዴ ሆምስ (TdH) እና ሳይሴትቨርስ( Sightsavers) አማካሪን ጨምሮ ሶሻል ዲቨሎፕመንት ዳይሬክት (SDDirect) የቴክኒክ ነክ እና የአቅርቦት መሪ ሆኖ፣ በኦፕሽንስ በሚመራ አጠቃላይ ህብረት ይሰጣሉ።

**የኤክስፐርቶች/የባለሙያዎች ምክር ተጠይቋል፣ ድርጅቶቹም፦** አንጂ ባምቦሴ (Angie Bamgbose)፣ ከጂሲፒኤስ አማካሪ ድርጅት (GCPS Consulting) ፡፡

**ማጣቀሻ/ዋቢዎች ፦** Bamgbose A (2021) የማዋከብ/ጉልቤነት እና ትንኮሳ መግለጫዎች። የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል (RSH)፣ ለንደን፣ ዩናይትድ ኪንግደም፡ የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከል (RSH)